## ግልፅ ደብዳቤ

# ለብፁዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ

## ፓትርያርክ ካቶሊኮስ
## ፓትርያርካል ፓላስ
## አራት ኪሎ (ትንሽዋ ቫቲካን ሲቲ)

(እጅጉ ረታ)

«ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ

በቅድሚያ የማክበር በሰላምታዬን አቀርባለሁ። ከምድረ አሜሪካ በርረው መጥተው፣ በመጥፎ አጋጣሚ የፓትርያርክነቱን መንበር ከተረከቡበት ጊዜ አንስቶ፣ በዚች ምስኪን ቤተክርስቲያንና ለአባት ባልታደልነው በእኛ በልጆቿ ላይ የፈፀሙትና አሁንም በመፈጸም ላይ ያሉት



እኩይ ድርጊት ሁሉ፣ ከዚህ በፊት በነበረው በቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማያውቅ ነው- ፍጹም እንግዳ ነገር።

በ«ወቅር ትንፋሽዎ» አዝዘው ባስጻፉት መድሐፍ፣ ርትእት ሃይማኖቷን በኑፋቄ ትምህርት በክለዋል። (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ ጥር 1988 ዓ.ም በእንግሊዝኛው ክፍል ገጽ 15 ላይ ይመልከቷ)፤

ለዘመናት ጸንቶ የኖረውን ደገኛ ስርአቷን አፋልሰዋል፤ ዝቅ ብዬ አንድ በአንድ እመ ለሰበታለሁ- ከነማስረጃው።

የተቀደሰውን መንበሯን ደፍረው አስደ ፍረዋል- አንደኛውን ግልፁን ለመናገር ለምን አርክሰውታል አልልም? ይህንንም ዝቅ ብዬ አቀርበዋለሁ- በሚያጠግብና በሚያሳምን ኹናቴ ገልጬ።

በሌላም በኩል ብልሹ አመራርዎ በማና ለብኝነት እኩይ የአስተዳደር በደል ፈጽሟል።

ለኃላፊነት የማይበቁ መናኛና አልባሌ ሰዎችን እየመረጠ ደህና- ደህና ቦታ በማስቀመጥ ከተራ ሌብነት ባላነሰ መልኩ የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ መዝብረዋል፤ አስመዝብረዋል፤ አባክነዋል፤ አውድሟል፤ እድገት ልማቷን አጨናግፏል- ያሳባት።

ይህ በአምባ ገነንነት፣ በማናለብኝነት የተፈጸመው እኩይ ድርጊት ሁሉ፣ ያን ጊዜውኑ ተነግሮአል፤ ተጽፏል፤ ተተችቷል። ሰሚ ያልተገኘም እንጂ፣ የታረመ፣ የተሻሻለ፣ የተለወጠ ነገር የለም፤ እንዲያውም ባሰበት እንጂ- በጎ ፈቃዱ ስለሌለ። የተነገረው፣ የተጻፈው ሐሰት ነው ከተባለም ማስተባበል ያባት ነው- ግዴታ! ራስን ነጻ ለማውጣት። አለማስተባበል ወይም ማስተባበል አለመቻልማ- በሕጉ መሠረት- እም ኖ እንደ መቀበል ይቆጠራል- በዝምታ።

ይህን እንዲያው ለነገሩ ያህል አልኩለት እንጂ ላስተባብልስ ቢሉ ምኑን ያስተባብሉታል? የመጽሐፉ ማስረጃ በመጽሐፍ፣ የሰነዱ ማስረጃ በሰነድ፣ የሰው ማስረጃ በሰው እሉ- ሁሉም ዝግጁ። የታጣው ቀናና ቤተ ክርስቲያኑን የሚያስከብር ጠንካራ መንፈሳዊ አካል ብቻ ነው- ጉዳዩ የሚል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ ይህ ሁሉ እኩይ ድርጊት ሲፈጸም መካሪ ዘካሪ አልታጣም ነበር፤ ግና ማን ሰምቶ?

ከውስጥ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱ አቡነ ዮሴፍ፣ አቡነ ጢሞቴዎስ፣ አቡነ ገብርኤል ለየብቻም በአንድነትም- ሆነው ሲሉቹንም የቅዱስ ሲኖዶሱን አባላት ይዘው ይኼ ፈሩን የሳተው አመራርዎ ትክክለኛ መስመሩን እንዲከተል፤ ግና ከመጀመሪያው አንስቶ አሳስበዎታል፤ የተፈጠረውንም ችግር በጥሞና በመወያየትና በመግባባት እንዲያስወግዱት ነግሮዎታል፤ ለምነዎታል፤ ተማጽነዎታል- ግና እርስዎ መች የሚሰሙ ሰው ሆኑና።

በመጨረሻም አምባ ገነንነትዎ እያየለ እየበረታ ሲሄድ፣ የባሰ ጉዳት ከመድረሱ በፊት የቤተክርስቲያኒቱ አካል፣ ዋና ክፍል የሆነው ሕዝበ ክርስቲያን (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 9/296 ይመለከቷል) እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ መስሎ ስለታያቸው፣ ነገሩን ይፋ አድርገውታል- በማስሚዲያ።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያኑ አለቃ አያሌው ታምሩ፣ መምሕር ሃብተማርያም ተድላና ሌሎቹም ሃቀኛ የሆኑ የትግራይ ተወላጅ መምሕራን ቤተክርስቲያን ሕገ ሃይማኖት ተጣሰ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፈረሰ ብለው እንዲታረም እንዲስተካከል አሳስበዎታል፤ ለምነዎታል፤ አል ሆነም- እንዲያውም እልህ ያዘዎና ጥርስዎን ነከሱባቸው እንጂ።

ከውጪም የተፈጠረው ችግር ክፉኛ ያሳሰባቸው ምዕመናን፣ ለምድር ለሰማይ በከበዱ አረጋውያን ተወካዮቻቸው አማካይነት ጠብ ጥላቻ እንዲቀር፣ ሰላም መግባባት እንዲፈጠር ለመኑዎ፤ ተማጸኑዎት- ግና ማ የከመጤፍ ይህል ቆጥሮአቸው? «የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እናንተን አይመለከታችሁም» አሰኝተው መለሷቸው-ተገጠው፤ ትልቅ ስሕተት።

ርእሰ ሊቀ ሊቃውንት መስፍን ወልደ ማርያም፣ ርእሰ ሊቀ ሊቃውንት ታደሰ ታምራት ብልሹ አመራርዎ፣ በግትርነት የተከተለው መንገድ አደገኛ መሆኑን አስቀድመው በማየት በጊዜ እንዲስተካከል፥ በፍርሃትና አክብሮት ያን ጊዜውኑ አሳሰቡ (አያቤተኛ ዓመት ቁ 2/1989 እና ቁ 10፣ 1990 ዓ.ም ጦቢያ መጽሄት ይምለከቷል) ኧረ ዲያ!! እነዚህ ደግሞ ያለስራቸው! ምን...ማከቆም ነገር ጥፏቸው!

በነገራችን ላይ «ካቶሊኮስ» የሚለው ባዕድ ቃል ትርጉሙ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ማለት እንደሆነ ሁሉ፣ ፕሮፌሰር የሚለውም ቃል ርእሰ ሊቀሊቃውንት በባል ያስኬዳል በሚል ነው ርእሰ ሊቀ ሊቃውንት የሚለውን የማዕረግ ስም በታላቅ አክብሮት ለምመለከታቸው ለነዚህ አድባር ምሁራን የቀጠልኩላቸው።

ሌላው ሰው፣ አብሮ አደግ- ባልንጀራዎ ናቸው- የቅርብ ወዳጅዎ። ብልሹ አመራርዎ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ሰምተው በመቆጨት ከምድረ አሜሪካ ድረስ መጥተው መክረዎታል፤ ዘክረዎታል- ዘመድ ወዳጅ ባለበት። «አባክዎትን የትግራይን ስም አያስነሱ» ብለው ተማጽነዎታል። ለነገሩማ እንኳን ከአሜሪካ ይቅርና መልአክ ከሰማይ ወርዶ ቢነግርዎ እርስዎ መች የሚሰሙ ሰው ሆኑና!! እርስዎን መምከር፣ ለእርስዎ መንገር ማለት በጣቁር ድንጋይ ላይ ውሃ ማፍሰስ ማለት ነው- አልሰሙአቸውም። እርስዎ አልሰማ አሉ እንጂ መካሪማ መች ጠፋ?

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርትክ ምን ጊዜም ምክር የማይሰማው፣ የማይታረመውና ከተሳሳተ መንገዱም ለመመለስ ፈቃዱም ፍላጎቱም የሌለው ብልሹ አመራርዎ፣ አበሳዋ ገና ያላለቀላትን ይቺን ምስኪን ቤተ ክርስቲያን ሲያምሳት፣ ሲያብጣት፣ ሲበጠብጣት እነሆ ዓስር ዓመት አለፈ።

ዛሬ በማሕደረ ስብሐት ቅድስት ልዴታ ለማርያምና በደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም ገዳም፣ በካህናቱ፣ በዲያቆናቱ፣ በሰበካ ጉባኤው አባላት፣ በሰንበት ት/ቤት ወጣቶችና በምእመናኑ ላይ እንዲያውም ለመንገደኛውና አርፎ እቤቱ ለተቀመጠው የአካባቢው ሕዝብ- እስላም ክርስቲያን ሳይለይ- የደረሰው እኩይ ድርጊት ሁሉ ከጭቁኑ ሚካኤል፣ ከጎፋ ገብርኤል፣ ከዑራኤል፣ ከራጉኤል፣ ከአደባባይ ኢየሱስ፣ ከእስጢፋኖስ፣ ከዮሐንስ፣ ከቅዱሴ፣ ከቦሌ መድኃኔ አለም፣ ከሐና ማርያም... የቀጠለ የብልሹ አመራርዎ ውጤት እንጂ እንግዳ ወይም አዲስ ነገር አይደለምና አያስደንቅም። እርስዎ በመንበሩ ላይ እስካሉም ድረስ የሚቀጥል፣ ለሌሎቹም የሚተርፍ መሆኑንም በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ ብልሹ አመራርዎ «ከበስተኋላ የተማመነው ተማም ኖ» እስካሁን የፈጸመውን ግፍና በደል፣ ደባና ተንኮል እዚህ ላይ በዝርዝር ማቅረቡ የሚያስፈልግ ሆኖ አላገኘሁትም፤ ምን ያደርጋል? የደፍን አገሩ ጆሮ የጠገበውን?? ዓላማዬ ይኼ አይደለም። የኔ ዓላማ ብልሹ አመራርዎ በማናለብኝነት

የጣሰው እያንዳንዱ እኩይ ድርጊት ከሐዋርያት... ከሰለስቱ ምዕት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያም መተዳደሪያም ከሆነው፣ ቅዱሳት መፃህፍትን መሰረት ካደረገው፣ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ድንጋጌ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ምን ይመስላል? የሚያስከትለውስ መንፈሳዊ ቅጣት ምንድን ነው? የሚለውን ቁም ነገር ማንሳት፣ ምእመናን ወገኖቹ እንዲያውቁትም ማቅረብ ነው፡፡ አዎን ምዕመናን ወገኖቹ ብቻ እንዲያውቁት ማቅረብ፡፡

ይኼን ቅዱስ ሲኖዶሱ እንዲያውቀው ለማቅረብ ግን ፍላጎቱም የለኝ፤ አልሞክረውምም፡፡ ልሞክረውስ ብል እንዴት አድርጌ? እንዴትስ ይሆንልኛል? ቀድሞ ነገር የብፁዓን አባቶቹን የጫማ ጠፍር ጎንበስ ብዬ መፍታት የማይገባኝ፣ እኔ እዚህ ግባ የማልባል አንድ ኢምንት የሆንኩ ሰው ማ ሆንኩና ነው ለእነርሱ የማቀርበው? ዕውቀቱስ መች አለኝና? ድፍረቱንስ ከየት አመጣውና...እነርሱስ የዚህን ሁሉ እኩይ ድርጊት መፈጸም መች አጡትና ነው እንግዲ ነገር፣ አዲስ ነገር አድርጌ ለእነሱ የማቀርበው፡፡

ሰነገሩማ «ቁሉም ዝም፣ መጽሐፉም ዝም አለ» እንደተባለው ሆኖ አውቆ ዝም ዝም አለ፤ አውቆ ተኝቦት እንጂ፣ ጥፋት በደሉንስ ቢሆን፣ ሕገ ቀኖናውንስ ቢሆን ቅዱስ ሲኖዶስ መች አጣውና? አውቆ የተኛን መቀስቀስ አይሁንብኝ እንጂ፣ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት አበው የተሰወረስ ምን ጥፋትና በደል ሊኖር? ከእነሱስ ወዲያ ሕገ ቀኖና አዋቂ ከየት ሊመጣ?- አልሞክረውም፡፡ እኔ የማቀርበው፣ እንደ እኔ ምንም ምኝ የማያውቁ ምእመናን ወገኖቹ እንዲያውቁት በማካባ እንዲረዱት ለማድረግ ብቻ ነው- እነሱ ብቻ፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እንግዲህ ወደ ዋናው ጉዳይ በቀጥታ ልግባና፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የኤጲስ ቆጶስነትን ምርጫ በተመለከተ ምን ይላል? (ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ተ.ቤ.ክ.ፍ.ም.አ.-5/93) ላይ፣ «ስለ ሃይማኖቱና ስለ ዕውቀቱ፣ ስለ አነጋገሩ፣ (ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ)፣ ስለመልካም ምግባሩ ሳይመረጥ (በሚገባ ሳይጤን ሳይመረመር) ኤጲስ ቆጶስነትን አይሾም» ይላል- ከዚህ ልጀምር፡፡

ታዲያ እርስዎ በዕጩነት የቀረቡት፣ ቀርበውም የተመረጡት መንበሩንስ የተረከቡት፣ ከዚህ በላይ የተመለከተውን የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ድንጋጌ በእርግጥ አሟልተው ተገኝተው ነው? መልሱ አይደለም ነው- ባጭሩ፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ነገሩ ገና በፊቱ የምር የታሰበት በመሆኑ፣ የዕጩነት መመዘኛው ካባ ላንቃ ለእርስዎ ብቻ እንዲስማማ፣ በእርስዎ ላይ ብቻ ልክክ እንዲል፣ በእርስዎ ልክ ተመተረ (ተለካ)፤ ተቆረጠ፤ ተሰፋ፡፡ «ቅዱስ ነትዎ»ም ያን ለበሱ፤ መንበሩን ተረከቡ፡፡ ይችን ጨዋታ እርስዎም፤ በዕጩነት ያቀረበዎትም ቡድን ልበል ክፍል/ሂደቱን በቅርብ ርቀት- በ ትዝብት የተከታለተውም ሁሉ አሳምሮ የሚያውቀው ነው፡፡

እንግዲህ ነገር የተበላሸው እዚህ ላይ ነው ገና ከመጀመሪያው፡፡ ለሃይማኖቷ መፍለስ ለቀኖናዋ መጣስ፣ ለአስተዳደሯ መበላሸት፣ ለምዝበራና ለብክነት ለሌላ- ሌላውም እኩይ ድርጊት ሁሉ ዋናው ምክንያት ይኸው ብቻ ነው፤ በሕጓ፣ በቀኖናዋ፣ በስርአቷ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱ እውነተኛ አባቷን መምረጥ አለመቻሏ -ነጾ ሆና፡፡ ለዚህ ሁሉ ግፍና በደል፣ ደባና ተንኮል የተጋለጠችውም ከዚሁ የተነሳ መሆኑን በግልጽ ማየት ይቻላል- ሥራ ምስክር ነው ተብሏልና፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፍትሐዊ ርትዓዊ አስተዳዳርን በተመለከተ ምን ይላል?

«ኤጲስ ቆጶስ ሆይ መድኃኒታችንን፣ ንጉሣችንን፣ አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት ልታደርገው ይገባል፤ እርሱን ምሰሉ፤ የምትራሩ፣ ሰላምንም የምትፈልጉ ትሆኑ ዘንድ...ትዕቢተኞች ፊት አይታችሁ የምታደሉ ኩራተኞች አትሁኑ...እናንተ አሁን ደጎች መጋቢዎች ሆናችኋልና፡፡ የሰጣችሁንም ስርአቱንና አስተዳደሩን ትመልሳላችሁና» (ፍ.መ.አ.5/126 ይመልከቷል) ይላል፡፡ በሌላም አንቀጽ (5/130)፣ «ልብህን አስፍተህ እንደ እግዚአብሄር ሰው ሁን» ይላል፡፡ አሁንም በሌላ አንቀጽ 5/114 ላይ «ለምእመናን በአነጋገር፣ በተጋድሎ፣ በፍቅር፣ በሃይማኖት፣ በንጽሕና አንተ አብነት ሁናቸው» ይለዋል- ኤጲስ ቆጶሱን፡፡ በነገራችን ላይ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ለኤጲስ ቆጶሱ የሚሠራው ህግ ለጳጳሱም፣ ለሊቀ ጳጳሱም፣ ለፓትርያሪኩም የሚሰራ መሆኑን ራሱ መጽሐፉ የሚናገር መሆኑን እዚህ ላይ መግለፅ ተገቢ ይመስለኛል- አንድ ነው፡፡ (ፍ.መ.አ.180 ይመለከቷል)፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እስቲ ልጠይቅዎ? ከዚህ በላይ እንደተመለከተው አንድ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊኖረው ከሚገባው ከቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ድንጋጌ- አይደለም ግማሹን፣ ሩቡን፣ አለኝ የሚሉት፣ እንዲያው አንድ እንኳ መልካም ነገር አለ? ለማለ ያህል?? አይመስለኝም፤ ሥራ እኮ ምስክር ነው፣ ቀድሞ ይናገራል፡፡

ታላቁን እረኛ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አብነት ያደረገ፣ አርአያነቱን ምሳሌነቱን የተከተለ፣ አይደለም ግማሹን፣ ሩቡን አለኝ የሚሉት እንዲያው አንድ እንኳ መልካም ነገር አለ?- ለማለ ያህል?? አላምንም፣ ሥራ እኮ ምስክር ነው፣ ቀድሞ ይናገራል፡፡

ለምእመናን በአነጋገር፣ በፍቅር፣ በሃይማኖት፣ በንፅሕና አብነት እሆናቸዋለሁ ብለው የሚመኩበት፣ አይደለም ግማሹን ሩቡን፣ እንዲያው አንድ እንኳ መልካም ነገር አለ? ለማለ ያህል?? ይህንንም አላምንም፤ ሥራ እኮ ምስክር ነው፣ ቀድሞ ይናገራል፡፡

«ልቤን እንደ እግዚአብሄር ሰው ያሰፋሁ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ አባት ነኝ» ብለውስ አይደለም አፍዎን ሞልተው በዚህ ሕዝብ ፊት መናገር፣ እንዲት ቃል እንኳ መተንፈስ ይችላሉ? አይመስለኝም፤ እስከዚህ ደፍረውም ያደርጉታል ብዬ አላምንም- ሥራኮ ምስክር ነው፤ ቀድሞ ይናገራል፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ አልሆኑም፤ አይደሉም እንጂ፤ እርስዎ የዓለሙን መድኃኒት እግዚእ ኢየሱስን አብነት ያደረጉ፣ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ አባት ቢሆኑ ኖሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከላይ እንስቶ እስከታች ድረስ እስከዚህ በልታመሰች፣ በልተናጠች፣ ባልተብጠበጠችም ነበር፤ ሰላሟን፣ ጸጥታዋን እስከዚህ ባላጣች ነበር፤ እስከዚህ የዋይታ የሰቆቃ ቤት ባልሆነችም ነበር፡፡

አንዱን ያለ ጥፋቱ፣ ያለ በደሉ በሚገባ ለብዙኃነት ከሥራ፣ ከደመወዝ ያገዱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያኒቱን ከስሶ መብቱን በፍርድ ያጣ ሰው ሽለተገናበስ ብቻ ያልሠራበትን የስምንት ዓመት ደመወዝ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ያላግባብ እንዲያገኝ ያደረገ ሰው እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ፣ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ አባት ነኝ ቢል፣ በፍትሐዊና በርትአዊ አስተዳዳር ላይ አፈዘ፤ ዘበተ፤ አላገጠ እንጂ እንደ ሉት ተደርጎ እውነተኛ የቤክርስቲያን መሪስ፣ አባትስ መሆን ይችላል?- ትልቅ ትዝብት!

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ብትምክርቱ፣ በዕውቀቱ፣ በአስተዳደር ችሎታው፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሳይሆን፣ ለእርስዎ ባለው ቀረቤታና የጥቅም ግንኙነት ብቻ «ኩንኖዬ» ያሉትን ሰው ብድግ አድርገው ደዐና ግንብ እም ትታለብበት በረት ወስደው ያኑታል፡፡ በጮጮ እያለበ ትኩስ ወተትዋን ነጋ ጠባ ለራሱ ይጠጣል፤ አይቡን ቅቤውን እያሰናዳ በእንስራ በማሰሮ እያጠራቀመ እጅ መንሻ ያቀርባል- ታዲያ ይኼ አበጀ፤ አሳመረ እንጂ ምናጠፋ?- እንደ ርስዎ.. እንደርስዎ፡፡ ካልተነቃበት እዚያው ይቆያል፤ ከተነቃበት ነገር ከከረረ የተሻለች ጥገት ወዳለችበት ደሞ በወፍራም ጭማሪ ይዛወራል፤ በምንም ዓይነት አይቀጣም፤ ከሥራ አይባረርም፤ ምን አደረገ? ምናጠፋ?

አዎን «አባታችን» የዓለሙን መድኃኒት እግዚእ ኢየሱስን አብነት አድርገው፣ አርአያውን ምሳሌውን ተከትለው፣ ልብዎን እንደ እግዚአብሄር ሰው አስፍተው፣ አብዝተው እንዲመልሱ የተቀበሉትን የምናን /አደራ/ ... ብረው፣ የሚመሩአት ቤተ ክርስቲያን እንግዲህ አዎን ይህቺ መሆንዋ ነው- የሌቦች ዋሻ የቀማኞች መሸሻ፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ቁጣን በተመለከተ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ምን ይላል? «የሚታገስ፣ በመልካም ስርአት ሁሉ የፀና ይሁን...ቁጡ፣ ገንዘብ ወዳጅ አይሁን፤ ጥበብ ቁጣ አዋቂዎችን ታጠፋለች ትላለችና (ምሳ.15፣1)፡፡ ሰውን አፍቃሪ ይሁን (የሐ.13፣ 35) ይላል» (ፍ.መ.አ.5/87 ይመለከቷ)፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ «ቅዱስነትዎ» በጣም ቁጡ፣ በጣም ተናዳጅ፣ እጅግ ሲበዛ አልኸኛና ግትር መሆንዎም በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው፡፡ ለዚህ ለቁጣኝነቱ፣ ለበቀለኛነቱ፣ ለጨካኝነቱ ዋና መነሻ ምክንያቱ ነገሮችን በእርጋታ ማየት አለመቻል፣ ትእግስት ማጣት፣ በቀዶ አሳት ተጥዶ መንተክተክ መፍላት ነው፡፡ ትእግስት የሌለው ቁጡ ሰው ደሞ እንኳን በሚሊዮን ቤት ለሚቆጠሩ ምዕመናን አባት ሆኖ፣ ቤተክርስቲያኒቱን በፓትርያርክነት ሊመራ ይቅርና፣ ጥቂት ሰዎች በመከፈልት ላይ ለሚሪዙ በት ለደጅ ሰላም አጋፋሪነት እንኳ ብቁ ሊሆን አይችልም፤ ይኼ ራሱ ብቻ እንኳ ትልቅ ግእግስት የሚጠይቅ ከባድ ሥራ ነውና፡፡ ታዲያ አበሳዋ ገና ያላለቀላት ይቺ ምስኪን ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሁኔታ የምትመራው እስከ መቼ ድረስ ነው?

ቂመኛነትን፣ በቀለኛነትን በተመለከተ ቀኖና ቤተክርስቲያኑ ምን ይላል? «ፈጽሞ ቂመኛ የሆነ ...ክብርን የሚወድ..ቂሙን የማይረሳ ቢሆን ከሹመቱ ይሻር፡፡ እርሱንም የሚመስሉት ሁሉ የተለዩ ይሁኑ (ዲኩኑ ወንጌሃ)» (ፍ.ተ.ሐ.ም.አ.52182) ይላል፡፡ በሌላም አንቀጽ (5/150) <u>በአስ ምርው ጉድለት ምክንያት</u> በቃልን የሚሻ ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር እርሱ አጲስ ቆጶስ አይደለም፤ በሐሰት ኤጲስ ቆጶስ ይባላል እንጂ፡፡ <u>ሹመቱም ከእግዚአብሄር ዘንድ የተገኘ አይደለም፤ ከሰው የተገኘ ነው እንጂ</u>» ይላል፡፡

(ወደ ገፅ 6 ዞሯል)

# ጴጥሮስ ሰብፁዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ

## ፓትርያርክ ካቶሊኮስ፣ ፓትርያርካል ፓሳስ

### ክፍል 2

ከእጅጉ ረታ

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ «ቅዱስነትዎ» በዚህች ሰሰባት ብልታደስች ቤተ ክርስቲያን ላይ ቢጀመር ሕንስተ በማናስበንነት የፈጸሙባት ግፍና በደል፣ ደባና ተንኮል «ከቀናና ቤተ ክርስቲያን ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ምን ይመስላል?» የሚለውን ቁም ነገር፣ ይኽ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው (ፍ.መ.አ 5/152፣ 9/296) ቀን የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ይኽ ክርስቲያናዊ ግዴታውን ከሚገባው በላይ እየተወጣ መብቱ በቅዱስነትዎ ጫማ ያሰባት የተረገጠበት የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆነው ምእመን እንዲያውቀው፣ ይልቁንም ይኸን አኩይ ድርጊት ሁሉ በማናስበንነት የሚፈጽመውስ ሰው ማ መሆኑንና የሕይወት ገጸታውንም ለማሳየት ለዘጋጅቷ ያቀረብኩት ጽሁፍ እንዳለ በአንድ ጊዜ ቢወጣ ነበር በማለ ነበር። ይሁን እንጂ መጽሄቱ ቋሚ ዓምድ ከፍቶ በተለያዩ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያስተናግዳቸው ሲሉት መጣጥፎች ስላሉ አልተቻለም፤ በቂ ቦታ ታጣና ስለዚህም በይቀጥላል መቅረቡ ግድ ሆነ፤ ፍሬ ነገሩ ይቀጥላል።

ለብፁዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ካቶሊኮስ
ፓትርያርካል ፓሳስ
አራት ኪሎ (ትንሿ ቫቲካን ሲቲ)
«ብፁዕ ወቅዱስ

ሴላም ሳክል፣ የመምህር ሃብተማርያም ተድላ ልጅ አስከሬን ከአፀደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይ ቀበር አስከለከሉ- በአባቱ ላይ ጥርስዎን ስለነከሱ ባቸው ብቻ - ሬሳ ታቅፈው እንዲጨነቁ። መጽሐፍ የሚነገረን በሰው ጭንቅና መከራ የሚደሰት ሰይጣን ብቻ መሆኑን ነው (ኢዮ.ምዕ .1 እና 2 ይመለከቷል) አይ አጬካከን!

ደሞ ሴላ ሳክል፣ በእርስዎና በሊቀ ሊቃውንት አያሌው ታምሩ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እንዲያበቃ፣ ዕርቀ ሰላም እንዲወርድ የሲኖዶሱ አባላት ብፁአን ሊቃነ ጳጳሳት አበው ቆመው ለምኑዎ። እርስዎ ግን እንደ መንፈሳዊ አባትነትዎ፣ «ይቅር ለእግዚአብሄር» ማለት ሲገባዎ ያውቂመኛ በቀለኛ ነዎትና፣ «የእሱን ነገር ለእኔ ተውት፤ ወህኒ ወርዶ ፕሮፌሰር አስራት ባለበት ያስተምራል». በማለት ለእኒህ ደካማ ዓይነ ስውር ወህኒ ቤት ተመኙላቸው- ዕርቀ ሰላሙም ቀረ። ይህ ብቻም አልበቃዎትም። ከነቤተሰባቸው ለረሃብና ለችግር አሳልፈው ሰጡአቸው። ምንም ጥፋት፣ ምንም በደል ሳይኖር ለኦርቶዳክሳዊት ሃይማኖታችን መፋለስ በመቅናታቸው፣ ለሥርአተ ቤተ ክርስቲያናችን መጣስ በመቆርቆራቸው ብቻ።

አሁንም ደሞ ሴላ ሳክል? ብልሹ አመራርዎ በልደታ- መድኃአለም ገዳም የፈጠረው ችግር በፍቅር፣ በሰላምና በመግባባት መንገድ እንዲፈታ ምዕመናኑ በተወካዮቻቸው አማካይነት ደግመው ደጋግመው ጠየቁዎ፤ ለመኑዎ፤ እርስዎ ግን ካገደዱ የሚመለሱ ሰው አይደሉምና አልሆነም። ነገሩ ከእጅ አፈንግጦ በመውጣት ፍ/ቤት ከደረሰም በኋላ እንደገና አጥብቀው ለመኑዎ፤ በቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት፣ በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱ አማካይነት ማለዱዎ፤ «አይሆንም ተውኝ፤ አታስቸግሩኝ፤ ነገሩን መንግስት ይዞታልና ተውኝ አታስቸግሩኝ» ብለው የዕርቀ ሰላሙን መንገድ ዘጉት።

ጌታ በወንጌል፣ «ወንድምህ ቢበድልህ ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅር በለው» (ማቴ.18፣22) ያለው ቃል፣ እንዲሁም ወንጌላዊው ቅ.ዮሐንስ በመልእክቱ፣ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው» (1 ዮሐ.3፣15) ያለው ቃል፣ ልቡን የማይሰብረው ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ መንፈሳዊ አባት ነኝ ሊል አይችልም- ፈፅሞ! ቢልም ተቀባይነት አያገኝም። ነገሩ «ሲርባ ጊዴ» ካልሆነ በቀር።



አሳስፈላጊ ልብስንና ምግብን በተመለከተ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ምን ይላል? ፍ.መ.አ 5/142፣ «ሐር ወይም ቀጭን ልብስ የሚለብስ ወይም በአገሩ ነዳያን ተርበውና ታርዘው ሳሉ፣ ልዩ ልዩ ጣዕም ባለው ምግብ ማድን (ማዕድን) የሚያስጌጥ ኤጲስ ቆጶስ፣ ኤጲስ ቆጶስ አይደለም» ይላል። በሌላም አንቀጽ (5/127)፣ «ኤጲስ ቆጶስ ከልብስና ከምግብ የሚበቃውን ያህል የሚወስድ ይሁን...ልብሱን አያሳምር፤ ሥጋውን ለመሸፈን የሚበቃውን ያህል ይውሰድ እንጂ፣ ሌላ ጌጥ የሚያስፈልግ አይደለም» ይላል-እንዲህ እያሳመረ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ይኼን ቁም ሳጥንዎን ያስጨነቀውን፣ ዛሬ ለብሰውት ነገ የማይደግሙትን፣ የወተት አረፋ የመሰለ ነጭ የሐር ቀሚስ ያላየ፣ ሞኝ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን፣ ይኼን የመላበሻ ክፍልዎን ያጣበበውን- አንድ አይሉት ሁለት- ከሰላሳ በላይ የሆነ፣ ከነአላባሹ በወርቅ በአዕናቁ (በከበሩ ድንጋዮች) የተንቆጠቆጠ ዘውድ ያላየ፣ ከሞኝም ሞኝ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን፣ «ልብሱን አያሳምር፤ ስጋውን ለመሸፈን የሚበቃውን ያህል ይውሰድ እንጂ፣ ሌላ ጌጥ የሚያስፈልግ አይደለም» ይልልኛል። ምስኪን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን! አሰሁ መስሎታል፤ «ቅዱስነትዎ» ከጫማዎ ሥር ረግጠው ዓፈር ዲቤ እንዳስጋጡት አላወቀ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እዚህ ላይ የፈጸሙት ትልቁ በደል፣ እንዳይለብሱት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተከለከለውን የልብስ ዓይነት መልበስዎ ብቻ አይደለም፤ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ክብር የሚጨምረው፣ ወይም ለመንፈሳዊ ሕይወታቸ የሚፈይደው አንዳች ነገር ለሌለው፣ ለዚህ የግብዝነት ባሕርይ መገለጫ ለሆነው - ዕቃ... ዕቃ... የልጆች መጫወቻ (ዶቃ)- ብልጭልጭ ነገር የፈሰሰው፣ በሚሊዮን ቤት የሚቆጠር ዶላርም ሌላው በደል ነው-- ምዝበራ።

ከአንድ ትሑት የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባት ይልቅ፣ አንድ አስፈሪ ንጉሥ ነገሥት ለሚያስመስልዎ፣ ለዚህ ዘውድና ካባ ላንቃ የወጣው አንድ አገር ዶላር ስንቱን የታረዘ፣ የተራቆተ ትከሻ ባለበሰ፣ ስንቱንስ የተራብ ጎን ባነገ ነበር።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ይኼን የሄሮድስ አግሪጳን አርድ- አንቀጥቅጥ ልብሰ መንግሥት የመሰለ ካባ ላንቃዎን ተጭብሰው፣ ይኼን በወርቅ በአዕናቁ ያበደ ዘውድዎን ደፍተው፣ አርዌ ብርትዎን ወይም በትረ ጵጵስናዎን ጨብጠው፣ በተቀጸል ጽጌ ወይም በደመራ ወይም በጥምቀት ክብረ በዓል ወይም በበዓለ ንግሥ ዓውደ ምሕረት ላይ ጉብ ብለው በማይዎ ጊዜ ትሁት ነፍስ ያደረችበት የአንድ መንፈሳዊ አባት የተቀደሰ ሕይወት➔

ከውስጥዎ እንደ ጢስ ተኖ፣ እንደ ትቢያ በኖ ይጠፋብኝና በምትኩ የፈረንሳዩ ንጉሠ ነገሥት የቀዳማዊ ናፖሊዮን ስዕል ከፊቴ ገጭ ይልብኛል።

አምን ፎቶግራፉን በክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ስላሴ «ጎሕ ጽባሕ» መጽሐፍ ላይ ያየሁት፣ ያ፣ ዘውዱን ከፓፓው እጅ በቁጣ ያስጣለ፣ ራሱም ላይ በገዛ እጁ የጫነ፣ የዓፄ በጉልበቱ የናፖሊዮን በናፓርት ዕብሪት፣ ድፍረትና ማን አለብኝነት ሥዕል ከፊቱ ይመጣና ድቅን ይልብኛል። ነገሩን ስለ አጽንኦተ ነገር እንደገና ልድገመውና፣ እርስዎን እዚሁ እፊቴ ገብ ብለው እያየሁዎ፣ የማየው ግን እርስዎን ሳይሆን፣ ዓፄ በጉልበቱ ናፖሊዮንን፣ ዕብሪቱን፣ ድፍረቱንና ማናለብኝነቱን ነው- በእርስዎ ውስጥ። አንድ ትሑት ነፍስ ያደረችበትን የመንፈሳዊ አባት የተቀደሰ ሕይወት አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም።

ይህን ከማንም በላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱና በዙሪያዎ ያሉ ሁሉ አሳምረው ያውቃሉ- እኔ ብቻ አይደለሁም፤ ግና ምን ማድረግ ይቻላል? ነገሩ «ሲርባ ጊዷ» ሆነ።

«አባታችን እንዲያው ለጨዋታ ያህል እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅዎ፤ የታላቁ ናፖሊዮን፣ የታላቁ ፍሬዴሪክ...የታላቁ እስክንድር ስም በገናናነት ሲነሳ ጥረታቸው፣ ዝናቸው ሲወሳ፣ እንዲያው አይነሽጥዎትም? «ወይኔ ሰውዬው!» ብለውስ እንደ መጸጸር አይቃጣዎትም? «እኔስ ብሆን ከእነሱ በምን አንሳለሁ?» የሚል ድምፅ ከውስጥዎ አይሰማዎትም? ምድብዎ ከእነዚህ ጋር ነውና የትልቅነት ምኞት እዚህ ላይ ብዙ ማለት ይቻል ነበር፤ ግና ይቅር- ምን ያደርጋል?

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እስረ ፍኖቱን (ግብሩን) ሳይከተሉ፣ ስሙን አላግባብ ወስደው የሚጠሩበት፣ እውነተኛውና ትልቁ አባት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፣ እንዲህ እንደ እርስዎ እያማረጠ የሚቀያይረው የተንቆጠቆጠ ካባ- ላንቃ ከነ ዘውዱ፣ የወተት አረፋ የመሰለ ነጭ የሐር ቀሚስ ይቅርና፣ ትከሻው ላይ የሚጥለው የረባ መደረቢያ እንኳ አልነበረውም። እንኳ የሚያማርጠው የወርቅ፣ የዕንቁ ዘውድ ይቅርና በራሱ ላይ የሚጠመጥመው የረባ ዕራፊ (ጨርቅ)፣ ለእግሩ የረባ የጠፍር ጫማ እንኳ አልነበረውም፤ እንዲኖረውም እስከዚህ የሚጨነቅ አባት አልነበረም። ቀድሞ ነገር ለዚህ ዓለም ተድላ ደስታ ቅንጣት ታህል ደንታ መች ነበረውና። «እኔ በዓለሙ ዘንድ፣ ዓለሙም በእኔ ዘንድ የሞተ ነው» የሚል ፍፁም መንፈሳዊ አባት ነበር። የቅዱስነትዎ ፍላጎት ግን የተገላቢጦሹ መሆኑን አድራጎትዎ ሁሉ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል- ፍፁም ዓለማዊ፣ የተድላ የደስታ ሰው ፍላጎት።

<u>ዕለተ በዓለ ሲመትን በተመለከተ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ምን ይላል?</u> (ፍ.መ.አ 5/101 እና 5/103) የጳጳሳት በዓለ ሲመት በዕለተ እሁድ ብቻ እንዲፈጸም ይደነግጋል፤ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በጽርሐ ጽዮን የወረደው በዚች ዕለት ነውና (ሐዋ.ም.2፣ 1-4)።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እስከዚህ የሚያደርስ ምንም ችግር ሳይኖር፣ እስከዚህም የሚያጣድፍ ምንም ነገር ሳይኖር፣ በዓለ ሲመተ ጵጵስናውን ባዘቦቱ ቀን መፈጸምን ምን አመጣው? ይህ እኮ ሌላይቱ ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው እንጂ፣ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት አይደለም። እርስዎን ሃይማኖቱ «እንዲህ ነው» ካለኙት ነገሮች እንደማስረጃ ሆኖ ከሚቀርብብዎ ክስ አንዱ ይኼ ነው። ይህን ደሞ ማስተባበል የማይችሉት ስለሆነ፣ እውነተኛ የቤተ ክስቲያኒቱ መሪም አባትም አለመሆንዎን ራስዎ በተግባር እየገለፁት ነውና፤ እንዴት የዚች ቤተክርስቲያን መሪ ሊሆኑ ይችላሉ?-ሥርዓቷን በማንአለብኝነት እንዲህ እያፈረሱ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን <u>በተመለከተ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ ምን ይላል?</u> «በዝሙት ወይም በስርቆት ወይም በሐሰት በመማል የተገኘ (ሰው) ከክህነቱ ይሻር...» (ፍ.መ.አ 9/319) ይላል። በሌላም አንቀጽ (9/372) «....ንጹሕ ይሁን፤ ነውር ባለበት በአንዱም ቦታ አይገኝ..» ይላል። አሁንም በሌላ አንቀጽ (10/406) ላይ «ከመነኮሳት ወገን ከሴት ጋር የሚኖር ይህ ሥራ ማለት (አብሬ መኖሬ) ድል አይነሣኝም የሚል ሁለቱም ይለያዩ፤ ወይም የተለዩ (የተወገዙ) ይሁኑ። መጽሐፍ፣ «በጭኑ እሳት ቋጥሮ የማይቃጠል ማነው? (ምሳሌ 6፣ 27)። ቅዱሳት መጻሐፍትም ፈጽሞ ሴትን ከመቅረብና ከመነጋገር እንርቅ ዘንድ ያስተምሩናል (1ቆሮ 7፣ 1)» ይላል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እነዚህ አንቀጾች በእርስዎ ሕይወት ላይ በግልጽ ታይተዋል። እነሆ የክህነ መለያ፣ መታወቂያ የሆነውን የጽጽስና አክሊልዎንና የማዕረግ ልብስዎን አውልቀው ጥለው፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑ (ፍ.መ.አ.23/813) ካህናት የወታደር ወይም የሲቪል (የጨዋ) ልብስ እንዳይለብሱ የሚከለክለውን ድንጋጌ በማንአለብኝነት ተላልፈው፣ ዓለማዊ ልብስዎን ግጥም አድርገው በሁለት የፈረንጅ ቆንጆች መካከል ሆነው በመዝናኛ ስፍራ የተነሱት ፎቶግራፍ፣ በምስጢር ከተቀመጠበት ሾንጣዎ አፈትልኮ በጋዜጦች ዓምድ ላይ እንደ ዓመት በዓል ብቅል ተሰጥቶ አይተነዋል። ይህ ሥዕም ለቤተክርስቲያኒቱ ትልቅ ውርደት ነው፤ የተቀደሰውን መንበሯን መዘባበቻ ያደረገ፣ የምእመናን ልጆቿን አንገት ያስደፋ፣ አሳዛኝም አሳፋሪም ድርጊት።

ይኼም ብቻ አይደለም፤ እጅግ በጣም ዘመናዊ የሆነ ቴፕ ሪኮርደር፣ አንዳች የሚያህል ቴሌቪዥን ከነዶክ ሃብቶ ገብ ባለበት፣ ማድረያዎም ልዩ ጽ/ቤትዎም በሆነው በፓትርያርካል ፓላስዎ፣ ውበት ደም ግባቷ ልብ የሚሰውር፣ እዚህ ቦታ ቀረሽ የማትባል የሰላሳ ዓመት ቆንጆ አግብተው የቤቱ፣ የምድረ ግቢው ሙሉ አዛዥ ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው? ምንስ ታስቦ? ምንስ ተፈልጎ?

ቁም ነገሩ እኮ ግድ መርፌና ክር ሆኖ እመጣ ኘቱ ላይ አይደለም፤ ቀድሞ ነገር ቀሚስ ያጠለቀች ሴት ምን ሲደረግ እዚያ ገብታ ነው።

አምን ከእርስዎ በፊት በነበሩት አራት ፓትርያርኮችና ከዚያም በፊት በነበሩት አንድ መቶ አስር ግብጻውያን ሊቃነ ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ተደርጎ የማያውቀውን፣ ይህን እንደ ቤተ መቅደስ ታፍሮ፣ ተፈርቶና ተከብሮ ከአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመት በላይ የኖረውን መንበር እነሆ ደፍረው አስደፍረዋል። ታዲያ እንዲህ ያሉ ሰው የዚች ቤተ ክርስቲያን መሪ፣ የዚች ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አባት ነኝ ማለት ይችላሉ? ልለፈው- ከዚህ በላይ ርቁ መሄድ አልፈልግም፤ ያሳፍረኛል እንጂ ብዙ ማለት ይቻል ነበር።

<u>ምእመናንን መናቅ፣ ማቃለል በተመለከተ ቀኖና ቤ/ክርስቲያኑ ምን ይላል?</u> እንዲህ ይነበባል፦ «ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሄርን ሕዝብ አቁልቁሎ (አዘቅዝቆ) ቢያያቸው፣ በሕይወተ ሥጋው ሳለ መልካም አይሆንለትም፤ ከሞተም በኋላ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ አይደረግለትም» (ፍ.መ.አ 5/152) ይላል። በሌላም አንቀጽ (9/296) «ኤጲስ ቆጶስ በቀሳውስትና በዲያቆናት ላይ አይታበይ፤ ቀሳውስቱም በሕዝቡ ላይ አይታበዩ፤ የቤተክርስቲያን አኗኗሯ እርስ በርሷ በመከባበር ነውና። ሕዝባውያን ከሊሉስ ኤጴስ ቆጳሳትና ቀሳውስት በማን ላይ ይሾማሉ?» ይላል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ይህን እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባዎ የምዕመናን ተወካይ የሆኑትን አረጋውያን በአፈ ቀላጤዎ፣ በሊቀ ጳጳሱ በአባ ገሪማ አማካይነት፣ «የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ እናንተን አይመለከታችሁም» አሰኝተው እንዲመለሱ አደረጉ።

ግፍና በደልን፣ ደባና ተንኮልን የተሞላው ብልሹ አመራርዎ አሁን በቅርቡ በማሕደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ ለማርያምና በደብረ መድኃኒት መድኃኔ አለም ገዳም ምእምናን ላይ ያደረሰውም እኩይ ድርጊት ሁሉ፣ ከዚሁ የቀጠለ እንጂ፣ እንግዳና አዲስ ነገር አይደለም፤ እርስዎ በመንበሩ ላይ እስካሉም ድረስ፣ ይኼ ንቀቱ፣ አዘቅዝቆ ማየቱ የሚቆም አይመስልም፤ አሁን ማ ይሙት ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይተዋል? እንደዚያ ማለት ነው- ይቀጥላል።

ታዲያ ብልሹ አመራርዎ፣ ምእመናንን እንዲህ እየናቀ፣ እንዲህ አዘቅዝቆ ቁልቁል እያየ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል ዋና ክፍል የሆነውም የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እንዲህ እየተናቀ፣ እንዲህ ቁልቁል እየታየ፣ መሪነትና ተመሪነት፣ አባትነትና ልጅነት ሊኖር፣ መፈቃቀር፣ መከባበርስ ሊቀጥል ይችላል? መልሱን ለእርስዎ ልተወው።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ብልሹ አመራርዎ ከፈጸሟቸውና ከሚፈጽሟቸው ስሕተቶች አንዱ ብቻ ሳይሆን ዋናው፣ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከመናቅ ከማቃለሉም በላይ፣ እንዳላዋቂ እንደ ደንቆሮ መቁጠሩ ነው - ትልቅ ስድብ።

«እኛ ያልንህን ብቻ መስማት፣ እኛ ያልንህን ብቻ መቀበል፣ ለጥ-ሰጥ ብለህ መገዛት እንጂ፣ የቤተክርስቲያኒቱ ጉዳይ አንተን፣ አይመለከትህም፤ አንተን አያገባህም» ማለት፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኑን በማናለብኝነት የጣሰ፣ ፍጹም እምቢተኝነት ነው- ራስንም ትዝብት ላይ የሚጥል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ከኪስዎ ወጥቶ የሚሰጠው፣ ወይም ከቤተ ክህነቱ ካዝና የሚላክለት ቤሳ ቤስቲን ሳይኖር፣ ከአለቃው እስከ ዘበኛው፣ ከቀዳሹ እስከ አወዳሹ ያለውን የየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን ደመወዝ ራሱ ችሎ የሚያስተዳድረውን፣ ይኼን ደግ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ የልማት የግንባታውን ሥራ ራሱ አውጥቶ በገንዘቡም፣ በጉልበቱም ደፋ ቀና የሚለውን፣ ይኼን እንኳን ገንዘቡን እጅህን ቆርጠህ ስጥ ቢሉት ቆርጦ ለመስጠት ቅር የማይለውን ቅን ፍጥረት፣ የክርስቶስ መንጋ፣ መናቅ አዘቅዝቆ ማየት ይገባል? እልፍ ተርፎም እንደ ሕጉ እንደ ትእዛዙ (ዘሌ 27፣ 30 ዘዳ 14፣ 22፣ ማቴ 22፣ 18-22) ዓሥራት (ከመቶ ዓሥር) ብቻ ማውጣት ሲገባው፣ ከአቅም በላይ የተጣለበትን ከመቶ ሃያ የፈሰስ ዕዳ ሳያቅማማ ሳያንገራግር «ይሁን እሺ» ብሎ በየአመቱ የሚገፈግፈውን ይኼን አይቆረቁሬ ምእመን፣ በፍቅር ዓይን፣ በደግነት ዓይን በማየት ፈንታ፣ ፊቃዱን «እሺ በጄ» ብሎ በመፈጸም ፈንታ፣ በንቀት አይን አዘቅዝቆ ማየት፣ ማስቆጣት፣ ማስበርገግ፣ ይባስ ብሎም የታጠቀ ኃይል አዝምቶ፣ በጭካኔ በትር እንዲቀጠቀጥ ማድረግ ምን ይባላል? ይህን አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነኝ የሚል ሰው ይቅርና ማንስ ያደርገዋል? ያደርገዋልስ ተብሎ፣ እንኳን በእውን በሕልም ይታሰባል? እኩይ ግብር ነው፤ ፍጹም አረማዊ ድርጊት።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እስቲ ልጠይቅዎ፣ በቃለ አዋዲው መሠረት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት መምረጥ የሚችለው ምእመን፣ የራሱን አለቃ፣ የራሱን አስተዳዳር➔

እንዳይመርጥ ምን የሚከለክለው ነገር አለ? እለቃውን፣ አስተዳዳሪውን ራሱ ቢመርጥ የበለጠ ጥቅም እንጂ፣ ምንስ ጉዳት ያመጣል?

ሰባቱን ዲያቆናት የመረጣቸው ማነው? ማንበረ ምእመናኑ እንጂ፣ መች ሐዋርያት ናቸው? (የሐ.6፤3-6) ሐዋርያትማ፣ «የምትፈልጉአቸውን ሰዎች ራሳችሁ ምረጡና ስጡን፤ እኛ እንሾምላችኋለን» አሉ እንጂ፣ እንዲህ እንደ እርስዎ ሌላ ረብና ጥቅም ሽተው የፈለጋቸውን ሰው ራሳቸው መርጠው፣ ራሳቸው ሾመው በምዕምናኑ ላይ የግድ የጫና ማስቀመጣቸውን መጽሐፉ አይነግረንም።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እንዲያው ቢበልጡ፣ ቢበልጡ ሹመቱን ከራሱ ከጌታ በቀጥታ ከተቀበሉት፣ ከቅዱሳን ሐዋርያት አበው እርስዎ ይበልጣሉ? እንዲያው ቢበልጥ ቢበልጥ ቃለ ዐዋዲውስ፣ ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይበልጣል?

ፍትሕ መንፈሳዊስ፣ «ኤጲስ ቆጶስ በሚሾም ባቸው ሕዝቦችና በሊቀ ጳጳሱም ፈቃድ ይሁን። ድስቅ (መጽሐፍ ዲዲስቅልያ) 36 "ኤጲስ ቆጶስ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ፣ በሕዝብ ምርጫ ይሾም"» (አንቀጽ 5/90 እና 94) ይል የለምን?

ታዲያ ኤጲስ ቆጶስን ያህል የተከበረ አባት እንዲመርጥ ሕግ የተሠራለት ሕዝበ ክርስቲያን፣ የደጥቢያ ቤተክርስቲያኑን እለቃ እንዳይመርጥ መከልከል ይቻላል? እርስዎ ምን ቢበልጡ ቢበልጡ ከሰለስቱ ምእት፣ ቃለ ዐዋዲውስ ከፍትሕ መንፈሳዊ ሕግ ይበልጣል? ኸረ በፈጠረዎ ይሁንብዎ ይኼን ቅን ደግ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዳሻዋቂ፣ እንደ ደንቆሮ በመቁጠር አይጫወቱበት እንጂ። «አባታችን» የተከተሉት እንዲህ ያለውን የተሳሳተ መንገድ እኮ ነው፣ በልደታዎች ላይ አሁን በቅርቡ የወረደባቸውን፣ ያን ሁሉ መዓት ያመጣባቸው። ሌላማ ምን አጠፉ? ምንስ በደሉ? እመለስበታለሁ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ፣ እንዴት እንደ ሆነ እንጃ፣ እዚህ ላይ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ይኼን ነፍሱን በነጣላው (በመሀረሙ) ጫፍ እንደ ቋጠረ አምባገነን መሪ፣ ለከሙ ቅስፈት (ቅጽበት) በጥይት በሚቀልቡ ስውር ታጣቂዎችና አንጋቾች ታጅበው መውጣት መግባትዎን ሳየው፣ ይኼን ራሱንም፣ ሌላውንም ልመን ቢል እንኳ ማመን እንደማይችል አምባገነን መሪ ሁሉ፣ በዚህ ጥይት የማይበሳው ነው በሚባልለት፣ ወደ ውጪ እንጂ ወደ ውስጥ በማያሳይ ሽንጣም አውቶሞቢል ወይም ሽፍን ፓጃሮ ውስጥ፣ ጥግ ይዘው እየተጨነቁ መሄድዎን- በአይነ ኅሊና- ሳየው፣ «ወይኔ ደቶ ረታ ልጅ» እልና እገረማለሁ።

መገረም ብቻም አይደለም፤ እታዘብዎትና፣ «እንዲያው እኒህ ሰው» እላለሁ፣ በዙሪያው ስንትና ስንት ጠላት የነበረውና መላ ዘመኑን በጦርነት የፈጀው ንጉስ ዳዊት፣ «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ ክፉን አልፈራም፤ አንተ ከእኔ ጋር ነህና» (መዝ.22፤4) ያለውን አላነበቡትም? አያውቁትም ወይስ አያምኑትም? እላለሁ። እንዲሁም እግዚአ ፀባኦት አምላክ በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ፣ «አትፍራ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና፤ አትደንግጥ እኔ አምላክህ ነኝና» (ኢሳ.41፣ 10) ያለውንስ አላነበቡትም? አያውቁትም ወይስ አያምኑትም? እላለሁ።

ይልቁንም፣ መቼም በልጅነት የያዙት ቀለም አይረሳምና፣ በዲቁና ገብቶ ያቃጨለ ሰሞነኛ ሁሉ፣ «ኢትፍርህዎ ለሞት ፍርኅዎ ለኃጢአት» በማለት የሚያዜማትን የ«እሴብሕ ጸጋኪን» አዝማችስ ረስተውታል? አያውቁትም ወይስ አያምኑበትም? እልና እገረማለሁ።

«አባታችን» ይኼን ፍርሃቱን፣ በታጣቂ፣ በአንጋች መታጀቡን፣ በደርጉም ፓትርያርክ ላይ አይቸዋለሁ፤ የእርስዎ ግን ይበዛል፤ እንዲያውም ነፍሱን በመሀረሙ ጫፍ ላይ ከቋጠረውም ዓምባገነን መሪ የእርስዎ ይብሳል።

ፍርሃት ደግሞ ከሃይማኖት ጉድለት፣ የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ አጥብቆ ከመሻትና ከመውደድ የተነሳ የሚመጣ ክፉ ደዌ ነው፤ ታዲያ ምኑን የክርስቶስ ተከታይ ተሆነው? ምኑንስ ፓትርያርክ ተሆነው? ይህ፣ ይህ እንግዲህ የሚያሳየው «ቅዱስነትዎ» እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ፣ እውነተኛም መንፈሳዊ አባት አለመሆንዎን ነውና፣ ምናለ መንበሩን በገዛ ፈቃድዎ ቢለቁ? በእግዚአብሔርም ቤት ባያላግጡ?..

<u>አፍቅሮ ንዋይን በተመለከተ</u> ቀኖና ቤተክርስቲያኑ ምን ይላል?

« ኤጲስ ቆጶስ የሚያሳፍር የማህበርን ረብ (የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ) አይውደድ..አብልጡልኝ አይበል...ገንዘብ ወዳጅ አይሁን ...» (ፍ.መ.አ 5/111) ይላል። በሌላም አንቀጽ (5/115) ሕገ ቀኖናው የሐዋርያውን ቃል (1 ጢሞ.6 ፤5-21) እንዳለ አምጥቶ - እኔ ግን አልፌ አልፌ ብቻ አስገባዋለሁ- «ገንዘብ የሚወዱ፣ ለመበልጠግም የሚሹ ግን፣ ሰውን በፍጹም ጥፋት በምታሰጥምና በምታስት... ምኞት ይወድቃሉ፤ የክፉ ሥራ ሁሉ ምንጩ ገንዘብ መውደድ ነውና። እነሆ ብዙ ሰዎች ይህን ተመኝተው ከሃይማኖት ወጡ..» ይላል።

እዚህ ላይ ከሌላ ቦታ አምጥቼ ሌላም ጥቅስ ባስቀምጥ ደስ ይለኛል።

ካህሊል ጊብራን የተባለ ሊባኖሳዊ ስመጥር ጸሐፊ «He is a traitor who uses the Gosple as a threat to extract money../ a hypocrite who uses the cross as sword ../a wolf disguised in lamb's skin...» ይላል። ይህን በግርድፉ ወደ አማርኛችን ስመልሰው፣ «ወንጌልን የገንዘብ መመንተፊያ መሳሪያ ለማድረግ በማስፈራሪያነት የሚጠቀምበት፣ ከሃዲ ነው- የማይታመን ......መስቀልን እንደ ሰይፍ የሚቆጥረው አጉል አስመሳይ፣ እንዲሁም የበግ ለምድ የለበሰ ተኩላ... ነው» ይለዋል። (ባማርኛችን «የቀበሮ ባሕታዊ እበጎች መካከል ገብቶ ይሰግዳል» ብለን እንደምንተርተው ምሳሌ ማለት ነው)።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ሁለት ዓይኑን አገንዘብ ላይ ብቻ ተክሎ፣ ምዝበራና ሙስናን ስውር አጀንዳው በማድረግ፣ ያለ ይሉኝታ፣ ያለ ሃፍረት የሚንቀሳቀሰው ብልሹ አመራርዎ፣ የተላበ ሰውን የገጸ ባሕርይ ካባና ቀሚስ ምንነት፣ በትክክለኛ መልኩ ሥሎ ለማሳየት፣ ከዚህ የተሻለ ገለጻ ይኖር አይመስለኝም።

ቅዱስነትዎ እኮ ይቺን ቤተክርስቲያን የሚያዩአት፣ ብር በአካፋ እንደምታዝቅ፣ እንደ አንድ የግል ማምረቻ ድርጅት፣ ራስዎንም የሚመለከቱት ኑሮው፣ ትዳሩ እንደተሟላለት፣ እንዳማረለት እንደ አንድ የናጠጠ - ከጌታ አላሙዲን በላይ- ቱጃር የሆነ፣ ቀብራራ የስዑዲ ሀብታም እንጂ፣ እንዳንድ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዳንድ መንፈሳዊ አባት አለመሆኑን ነገረ ሥራዎ ሁሉ በግልጽ ያሳያል።

አሁን የዚቺን ያጣች የነጣች ምስኪን ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አፍስሶ፣ ይኼን ሁሉ ዘመናዊ ሽንጣም አውቶሞቢል ማቀያየሩ፣ በዚህ በብልጭልጩ ነገር ማጌጡ፣ ይኼን ክንድ የሚሰብር፣ አንዳች የሚያህል የወርቅ መስቀል መሸከሙ፣ ይኼን አንገት የሚያጎብጥ አንድ አገር አይከን ደርቦ ደርቦ ማንጠልጠሉ ምን ስሜት ይሰጥዎታል? ምንስ ክብር ይጨምርልዎታል? እንዲያው አይመካኝባትና ለቤተ ክርስቲያኒቱስ ክብር የሚፈይደው ምን ነገር አለ? በዛ....በዛ...በጣም በዛ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ በመጥፎ አጋጣሚ እጅዎ ላይ በወደቀችው በዚች ምስኪን ቤተ ክርስቲያን ላይ ለተፈጸመውና በመፈጸም ላይ ላለው ግፍና በደል፣ ደባና ተንኮል ሁሉ ዋናው ምክንያት ፍቅረ ንዋይ ነው - መጽሐፉ፣ «የክፋት ሁሉ ምንጭ» ያለው ገንዘብ የመውደድ በሽታ- ክፉ ደዌ። አዎን ምን ጊዜም ሊረካ የማይችለውና ከቶም ረክቶ የማያውቀው የገንዘብ ጥማት ሱስዎ ብቻ! ሌላ አይደለም።ዳሩ በሆሊውድ የፊልም ማእከል ገብተው ስልጣነ ክህነቱንም፣ራሱን ስጋሁ ወደሙንም ንቀው፣እቃለው በቅዱስ ቁርባን ተምሳሊት የተዘጋጀውን ክፍል (part)፣ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በተዋናይነት የተጫወቱ፣ ወይም መጫወቻ ያደረጉ ሰው፣ ለገንዘብ ሲሉ ምን የማያደርጉት ነገር አለ? እንግዲህ የቤተ ክርስቲያኒቱም መሪ የእኛም አባት እንዲህ ያሉት ሰው እርስዎ ነዎት ማለት ነው? እረ ስንቱ ተነግሮ ያልቃል?

ስንትና ስንት የልማት ሥራ ሊሠራበት የሚችለውን ገንዘብ፣ ስንትና ስንት ግዳጅ ሊፈፅም የሚችለውን ገንዘብ፣ «በታማኝ ሰዎችዎ» አማካይነት መዝብረዋል፣ አስመዝብረዋል፡- ፑዝርፊያ ያህል። ባጭሩ ተጫውተውበታል ማለቱ ይቀላል- ገንዘቡ ባለቤት እንደሌለው ገንዘብ ተቆጥሮ፣ ሃይ ባይ፣ ከልካይ ታጥቶ፣ ሁሉ በእጅዎ ሁሉ በደጅዎ ሆነና!- ምን ይደረግ? «ሲርባ ጊዲ»።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ባላገር ቆዳው ሞኝ መስሎ፣ ውስጡ ብስል አይደል? «ጠብቅ ያሉት ዝንጀሮ ክምር ሲንድ ተገኘ» አለ ይባላል- ሲተርት። የሚያሳዝነው፣ የሚያስቆጨውና የሚያስቆጣው፣ የተፈጸመው ምዝበራ፣ ሙስናና ሌላ ሌላውም እኩይ ድርጊት ሁሉ በእርስዎ መሆኑ ነው። በጎቹን ጠብቅ በተባሉት፣ የእግዚአብሔርንም፣ የቤተክርስቲያኒቱንም አደራ በተቀበሉት፣ በእርስዎ መሆኑ ነው። አዎን፣ በሌላ ሳይሆን፣ ወዲህ፣ «ዓለሙን ከነክብሩ ንቄአለሁ» ብለው የእንጦንስ- የመቃርስን ልብሰ ምንኩስና በለበሱ፣ በእርስዎ በአባ ገብረ መድኅን መፈጸሙ። አዎን ወዲህም ከጳጳስነት፣ ከሊቀ ጳጳስነት አልፎ ተርፎ «ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቀ ጳጳስ ዘ አክሱም፣ ወ ዕጨጌ ዘ መንበረ ተክለ ሃይማኖት» የተባለውን ከፍተኛውን የቤተ ክርስቲያኒቱን የማዕረግ ስም ደርበው፣ ደራርበው በተሸከሙ «በትልቁ» አባት፣ በዋናው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ በእርስዎ በራስዎ በአባ ጳውሉስ መፈጸሙ ነው ትልቅ ትዝብቱ።

«ብፁዕ ወ ቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ይኼን የተመዘበረውን፣በማናለብኝነት የባከነውን ሁሉ በዝርዝር ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፤ ምን ያደርጋል? አንድ ሁለቱን ብቻ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃ ይመስለኛል።

1. ራስዎ አዝዘው ያቋቋሙት የምርመራ ኮሚሽን በአስተዳዳር በደል፣ በዘረኝነት- ጎጠኝነት፣ በምዝበራ፣ በሙስና.. ወዘተ ስንትና ስንት ጉድ ገና ማውጣት ሲጀምር፣ እንዳይቀጥል በ«ወርቅ ትንፋሽዎ» አዝዘው ያስቆሙትን የምርመራ ውጤት ሰነድ፣

2. ከቤተ ክህነቱ ቁጥጥር ዋና ክፍል፣ ያላግባብ የባከነውን ገንዘብ በማስመልከት፣ ማንነቱን ገጭ አድርጎ ይፋ ያወጣውን ሰነድ፣ አዎን እዚህ ላይ በማስረጃነት ጠቅሶ ማለፉ ብቻ ይበቃ ይመስለኛል።

ሌላው ሳይወሳ መታለፍ የሌለበት አሁን በቅርቡ በወጣው የጥቅምት/ሕዳር 1995 ዓ.ም «ዜጋ» መጽሔት ላይ እንደተመለከተው ወጣ፣ ተብሎ ያላባት የተመዘበረውን ገንዘብ ልክ የያዘው ሰነድ➔

ነገድ፡2 የዞረ·

## ግልፅ ደብዳቤ...

([illegible])

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ አባ ሕርያቆስ ዘ ሃገረ ብሕንሳ ስለ ቅድስት ድንግል እመ ቤታችን ክብር በደረሰው መጽሐፈ ቅዳሴው ላይ «...በመኑ ወበ አምሳለ መኑ ናስተማስለኪ» እን ዳለው፣ የእርስዎን ቂመኛነት፣ የእርስዎን በቀ ለኛነት፣ ጨካኝነትና ክፋት በምን? በማንስ ልመ ስለው እችላለሁ? በኔሮን፣ በኢዲ አሚን በቢን ላደን እንዳልመስለው የእርስዎ በዛብኝ- የእን ጦጦን ተራራ አከለበኝ- የእነሱ አነሰብኝ- እዚህ ግባ የማልለው ኢምንት ነገር ሆነብኝ፣ ምክን ያቱም እርስዎ «ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ርእ ሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሊቀ ጳጳስ ዘ አክሱም፣ ወ ዕጨጌ ዘ መንበር ተክለ ሃይማኖት- ከክርስቲ ያኖች ሁሉ በላይ ክርስቲያን፣ የቤተ ክር ስቲያን መሪ፣ መንፈሳዊ አባት»፤

እነኔሮን፣ እነ ኢዲ አሚን፣ እነ ቢን ላደን ጌታ «በሠማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአችሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ...» (ማቴ.5፣44-45) ያለውን የትምህርተ ወንጌልን ጣዕም ያልቀመሱ፣ ደግሞም ሐዋርያው «ለማ ንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ... ራሳችሁ አትበቀሉ፤ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ "በቀል የእኔ ነው፤ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ" ይላል ጌታ... ክፉውን በመልካም አሸንፉ እንጂ በክፉ አትሸነፉ» (ሮሜ 12፣ 17-21) ያለውን ያል ተማሩ፣ ያልሰሙ፣ ያላወቁ ሰዎች- የሌላ ወገን፡፡

ታዲያ እንዴት ተደርጎ እርስዎን ከእነዚህ ሰዎች ጋር ማነጻጸር ይቻላል? «አባታችን» unfair! ከእነርሱ ይልቅ የእርስዎ ይከፋል- የትና የት! ላስረዳ፦

ታቦተ ሕጉ ወጥቶ በቆመበት፣ ምዕመናን ተሰብስበው በዓሉን በሚያከብሩበት፣ በሰማዕቱ በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የባሕታዊ ውን ንፁሕ ደም አስፈሰሱ፡፡ ለጥላቻው፣ ለቂሙ፣ ለበቀሉ፣ ለግፉ፣ ለበደሉ ይኸው ብቻ በበቃ ነበር፤ በዚህ ብቻ አልረኩም፤ እዚያው ቆመው ሬሳውን በወንበር አስቀጠቀጡ፤ ይኼም አልበቃዎትም፤ ሬሳው በአፀደ ቤተክርስቲያን እንዳይቀበር ከለከሉ፡፡ ይኼም ብቻ አልበቃዎ ትም እንደ ጲላጦስ «ከደሙ ንፁሕ ነኝ» ለማለት ድራማ አሠሩ፤ በቴሌቪዥን መስኮት ታየ- ትል ቅ ትዝብት፡፡

(ይቀጥላል)

ነገድ 5 የዞረ

ጉዳይ ነው፡፡

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ በዓለ ንግሥዋ በማነደረ ስብሐት ቅድስት ልደተ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን፣ ምን ጊዜም ተከብሮ በማያውቀው፣ በግንቦት 21 ማርያም ስም እርስዎንና ተከታይዎች ምን ለማብላት ለማጠጣት፣ ለቁርጥ ሥጋ፣ ለቡፌ፣ ለውስኪ፣ ለጠጅ፣ ለቢራ ተብሎ «በታማ ኞችዎ» እጅ የወጣው ብር ሰላሳ ሺህ ትዝብት ላይ አይጥልም? ይህ ምዝበራ ነው መባል ያለበት? ወይስ ተራ ሌብነት?- አሳፋሪ ድርጊት፡፡

እንዲያው፣ እንዲህ እንዲህ ያለ አሳፋሪ ነገር ሲደርስ፣ ሲያጋጥም ከቤተሰብ፣ ከቤተዘመድ ወይም ከባለሟሎችዎ ደፈር ብሎ፣ «የለም አባታ ችን! ይኼ፣ይኼ እኮ አጉል ነው፤ ስም ያስነሳልና ይቅር...» የሚል አንድ እንኳ ሰው ባጠገብዎ የለም? ወይስ እንዲያው ሁሉም በጅብ ቆዳ የተጠ ፈረ ከበሮ ነው- እንብላው....እንብላው......ብቻ የሚል፡፡

ይህ እንግዲህ የአንዱ ቦታ ጉድ፣ የልደታ መድኃኒዓለም ገዳም ብቻ ሲሆን፣ አብልተ በይ ታማኞችዎ በተሰገሰጉባቸው በሌሎቹ ገዳማት፣ አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት ባሙት በዓል፣ በክ ብረ በዓል ስም እየተመካኘ፤ በየጊዜው የሚመዘበ ረው ገንዘብ፣ ስንትና ስንት መሆኑን በዚሁ ብቻ መገመት ይቻላል፡፡ ከምኑም ከምኑም ነጻ የሆነ የውጭ ኦዲተር ገብቶ የቤተ ክህነቱን፣ የልማት ኮሚሽኑን፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑን ወዘተ ሰነድ ገቢና ወጪ በትክክል ቢመረምር ስንትና ስንት ጉድ በወጣ -የሚያስተዛዝብ፡፡

የዛሬው እዚህ ላይ ያብቃ- ሌላውን በሌላ ወቅት እመለስበታለሁ፡፡■

# ይድረስ ለብፁዕ ወቅዱስ አባ ጳውሎስ

## ፓትርያርክ ካቶሊኮስ፣ ፓትርያርካል ፓፓስ (ትንሽዋ ቫቲካን ሲቲ)

### ክፍል 3

እጅጉ ረታ

ከየካቲት እና ከመጋቢት 1995 ቅጽ 4 ቁጥር 044/95 እና ቁጥር 045/95 ኢትኦጵ መጽሔት ላይ ለቅዱስነትዎ የጻፍኩትን ግልጽ ደብዳቤ ካነበቡ ሰዎች በዝግጅት ክፍሉም በኩል፣ በቀጥታም የተለያዩ አስተያየቶች ደርሰውኛል- ከማውቃቸው ወዳጃጆቼም፣ ከማላውቃቸው ወገኖቼም፣ በግንባር ካገኙኝ፣ በስልክ ካነጋገሩኝ አብዛኞቹ በእኔ ስሜታቸውን በአንክሮ ገልጸውልኛል:: «እ..እ...ሰውየው ክፉ ጨካኝ ናቸውና አንድ ነገር እንዳያደርጉብህ አደራ ተጠንቀቅ» ያሉኝም አሉ- ስለ እኔ በመስጋት፣ በመጨነቅ- እርሱው ባለቤቱ ይጨነቅላቸውና:: በሌላም በኩል «ኧረ ምንስ ቢሆኑ፣ ምንስ ቢያደርጉ አንተን ምን ያገባሃል! አንከሳ! ቆይ ጠብቅ ግዴለም» ያሉኝም ሰው አለ:: ነገር ነገሩ ዛቻና ማስፈራራት መሆኑ ነው - የሚፈራ ሰው ተገኘና:: ባለቤቱ ይቁር ይበላቸው፣ ቀን ልቦና ይስጣቸው፣ ሌላ የምለው የለኝም:: እኒህ ሰውዬም ይህን ያህል ሊያስፈራሩኝ የምከሩት ግን ማን መስያቸው ይሆን? ወይ አለማወቅ::

«ብፁዕ ወ ቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እንግዲህ ወደሰረነገሩ ልመለስና፤ አሁን በቅርቡ በልደታ- መድኃኔዓለም ገዳም ካህናት፣ ዲያቆናት፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችና የአጥቢያው ምዕመናን ላይ በተከታታይ ለወረደው ለዚያ ሁሉ የሰቆቃ ዙር መዓት፣ ለዚያ ሁሉ እስራቂና ዘግናኝ የጭካኔ በትር ዋናው ምክንያት- ባለፈው እትም እንደተገለጠው - መጽሐፍ «የክፋት ሁሉ ምንጭ» ያለው ገንዘብ እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?- የእር ስዎ አልጠግብ ባይነት::

«ከእንግዲህስ አንምኝም፣ ያለፈው የተበላው ገንዘባችን ይበቃል» አሉ እንጂ፣ ልደታዎች ምን አጥፍተው? ምንስ በድለው ነው ለዚያ ዓይነቱ መከራና ስቃይ አሳልፈው የሰጧቸው?

«ከእንግዲህስ ልማደኞቹን የሙዳየ ምጽዋት ቀበኞችዎን አንቀበልም፣ ከእንግዲህስ ለልማት ለግንባታ ያዋጣነውን ገንዘብ ለቀን ጅብ አሳልፈን አንሰጥም» አሉ እንጂ ልደታዎች ሌላ ምን አጥፍተው? ምንስ በድለው ነው? በጭካኔ በትር እንዲቀጠቀጡ አሳልፈው የሰጧቸው?

ከዚያ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ፍትሐዊ፣ ርትአዊ አስተዳደር በማስፈን፣ ከዚያ በፊት ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ የልማት፣ የግንባታና የእድገት እቅድና ፕላን ዘርግተው የምእመናኑን እምኔታና ክበሬታ ያገኙትን መምህራችውን፣ አለቃቸውን፣ «አባክዎ አያንሱብን፣ ሰላም አያምጡብን» ብለው ለመኑዎ፣ ተማጸኑዎ- ከአንዴም ሁለት ሰስቴ:: በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳቱም አማካይነት አስለመኑዎ እንጂ፣ ልደታዎች ምን አጠፉ? ምንስ በደሉና ነው ያን ሁሉ መከራና ስቃይ ያመጡባቸው?

ቅዱስነትዎ ግን ከፍቅርና ከሰላም መንገድ ይልቅ በመንግስት ክንድና ጡንቻ ተመኩ፣ እንደ ትምም ራስ ቅቤ ጠጣ።

«ብፁዕ ወ ቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እስቲ ልጠይቅዎ ለልማት ለግንባታው ሥራ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ራሳቸው አዋጥተው፣ ራሳቸው ደፋ ቀና ከሚሉት ከራሳቸው ከልደታ- መድኃኔ ዓለም ገዳም የአጥቢያ ምእመናን ይልቅ እዚያ ላይ ያሉት አንድ ሰው እርስዎ ለልደታ- መድኃኔ አለም ገዳም ልማት፣ ግንባታና ዕድገት ይበልጥ አሳቢው እኔ ነኝ ቢሉ አሁን ማን ይሙት እውነት ይመስላል? ይህን እንኳን ቁስለኛቹ ልደታዎች ይቅሩና ሌላው ስ ቢሆን ያምናል? ይቀበላል?

«ብፁዕ ወ ቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እብልቶ በይ ታማኝ የሙዳየ ምጽዋት ደፊዎችዎ ከዘራፊነት ባላነሰ መልኩ የሚፈፅሙትን ሙሰናና ምዝበራ በተጨባጭ ማስረጃ ያረጋገጠው የጥቢያው ሕዝበ ክርስቲያን፣ ለልማት ግንባታው ሥራ አዋጥቶ በባንክ ያስቀመጠውን ሰባት ሚሊዮን ብር ሲያሲዙበት አሁንማ ይሙት «ቅዱስ አባታችን ይህን ያደረጉት እኮ ለእኛ ብለው ነው» ይላል ብለው ያስባሉ? እስከዚህ ራስዎን ያታልሉታል ብዬ አላምንም።

አለቃውን ሲያነሱበት፣ ገንዘቡን ሲያሲዙበት ይኼ ሁሉ ግርግር ጭብጦውን ለመቀማት መሆኑን ሕዝበ ክርስቲያኑ ገና ድሮውኑ ገብቶታል፣ ችግሩ ማስጣል አልቻለም እንጂ።

አዬ አንቺ ገንዘብ! አዬ አንቺ ሰባት ሚሊዮን ብር! ምክንያተ ስህተት ሆነሽ ያን ሁሉ መከራና ስቃይ በልደታ መድኃኔ አለሞች ላይ አምጥተሽልና እንደ ዕፀ በለሲቱ የተረገምሽ ሁኚ::

አዬ አንቺ በነዴማስ እጅ የገባሽ ሰባት ሚሊዮን ብር! ወዮልሽ ወዮታ አለብሽ! ደብዛሽ እልም ድርግም ብሎ ሲጠፉ ታይቶኛልና::

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ አይደሉም አልሆኑም እንጂ «ቅዱስነትዎ» እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ እውነተኛ አባት ቢሆኑ ኖሮ ቀድሞውኑ እስከ ፓትርያርካል ፓላስዎ የሚደርስ የምዝበራ፣ የሙስና መረብ ባልዘረጉም ነበር:: አይደሉም አልሆኑም እንጂ «ቅዱስነትዎ» እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ እውነተኛ አባት ቢሆኑ ኖሮ፣ ፍትሐዊ ርትአዊ አመራር በቤቱ በሰፈነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱም የሐዋርያውን ቃል (1 ቆሮ 6፡3-6) ጥሳ፣ እንዲሁም «ስለ ቤተ ክርስቲያን ሹማምንት የተሰራውን ሁሉ ወደዚህ ዓለም ገዥዎች አትውሰዱት...» (ፍ.መ.አ 9/301 እና 9/308) ያለውን ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አፍርሳ ወደ ዓለማዊ ፍ/ቤት ባልሄደች፣ ከሳሽም ተከሳሽም ባልሆነች፣ ሽንጧን ገትራም ሙግት ባልገጠመች ነበር- ትልቅ ትዝብት! ትልቅ ጥፋት!

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ አይደሉም፣ አልሆኑም እንጂ፣ «ቅዱስነትዎ» እውነተኛ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ፣ እውነተኛ አባት ቢሆኑ ኖሮ እንደ ይሁዳ መሪ ጠቋሚ በሆኑ «ታማኞችዎ» ግንባር ቀደምትነት ዘልቆ በገባ ኃይል አገር እማን ነው ብሎ ዛዘኑን፣ ብሶቱን በፀሎት በዝማሬ ለፈጣሪው በሚያቀርበው ምእመን ላይ እንደዚያ ያለ ዱብ ዕዳ እንዲወርድበት ደባ ባልሰሩበትም ነበር:: እኩይ ድርጊት እንኳ ቀን በቀን ያልደፈራት ቤተ ክርስቲያን በዘመን በትርክናዎ ከአንዴም ሁለት ሶስቴ ተደፈረች፣ ተዋረደች- ዕድሜ ለእርስዎ!

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ አይደሉም አልሆኑም እንጂ «ቅዱስነትዎ» እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ እውነተኛ አባት ቢሆኑ ኖሮ ማኅደረ ስብሐት ቀድሞውኑ እስከዚህ ባልታመሰች፣ ባልተበጠበጠች፣ ለሳማን ጸጥታዋን ባላጣች፣ የዋይታ የሰቆቃ ቤት ባልሆነችም ነበር፣ ለዚህ የሚያበቃ ጥፋት፣ በደል የለም እንጂ፣ ቢኖር እንኳ እንደመንፈሳዊ አባትነትዎ ነገሩን በጥሞና ይከታተሉት፣ በትእግስት ይይዙት፣ በፍቅር፣ በርህራሄ ዓይን ይመለከቱት ወደ በጎነት ይለውጡት ነበር እንጂ፣ እንደ ዓላውያን ነገስታት የታጠቀ ኃይል አያዘምቱባትም ነበር:: እንዲህ ያለው እኩይ ድርጊት ደግሞ፣ የእውነትና የጽድቅ ጠላት የሆነውን የዲያብሎስን ግብር የተከተለ እንጂ፣ የፍቅርና የትሕትና ባለቤት የሆነውን የክርስቶስን እርአያነት ምስሌ ያደረገ አለመሆኑ ይኸው በግልጽ እየታየ ነው።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ጌታ «በጎቹን ጠብቅ፣ ግልገሎቹን ጠብቅ» ያለውን አደራ፣ አባት ነኝ ባዩ «ቅዱስነትዎ» በልተው፣ በከበረው ደሙ የዋጃቸውን ልጆቹን አሳልፈው ሲሰጡት፣ አይደለም የአንድ ልደታ- መ/ዓለም ደብር፣ የአገር የሃያውን ደብር ምእመን፣ አይደለም በጎማ በትር፣ በመደሻ አናት እናቱን እየፈጠፈጠ ሬሳውን ለአራዊት ገዳም ቢሰጠው ፖሊስ ምን አጠፋ?

እንደ እውነቱ ከሆነ «በገዛ ደሙ ያዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን (ምእመን) ትጠብቋት ዘንድ፣ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (ሐዋ 20፡28) ያለውን አደራ አባት ነኝ ባዩ ቅዱስነትዎ እንክት አድርገው በልተው ልጆቹን አሳልፈው ሲሰጡት፣ አይደለም በደረቁ መላጨት፣ እንደ ቶማስ ሐዋርያ ሰውነት ቆዳቸውን ገፎ ስልቻ ቢያወጣው ፖሊስ ምን አጠፋ?

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ መቼም እንዴ ሆኗልና የመጀመሪያው ዙር ስቃይ «እሺ ሆነ» ይባል:: የሁለተኛውን ዙር መዓት ደግሞ ምን አመጣው? ነገር ካለቀ፣ ርክክብ ከተፈጸመ በኋላ፣ እንደ መንፈሳዊ አባትነትዎ አርአያ ምሳሌ ሆነው፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሰላም በፍቅርና በመግባባት መንፈስ መመለስ ይቻል ነበር- ግና አልፈለጉም:: መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ጠየቁ፣ ጠየቁ ልበል አዘዙ? አልዋለም አላደረም ያልታሰበ መዓት ወረደ::

የእርስዎ ማንነት መታወቅ አለበት፣ ኃይል →



ት— በግለሰ፡ የተገኘ፡

ስልጣንዎ መታወቁ፣ መረጋገጥ፣ የግድ ተቀባይነት ማግኘት አለበትና ቅስቀሳ የምትል ሰላ ቤተ ክርስቲያን ብትኖር- ልደታዎችን አይታ- ነገ ምን እንደሚደርስበት አውቃ፣ ሰጥ ለጥ ብላ እንድትገዛልዎ፣ «እኔን ያየህ ተቀጣ» ልደታዎች ዱብ ዕዳ ወረደባቸው- የመርፌ ቀዳዳ ታህል መግቢያ ተገኘና- ሰበብ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ስመሆኑ ከኢህአዴግ ጋር ያለዎት የፖለቲካ ዝምድና ደረጃው እምን ድረስ ነው? ሞኝ አይበሉኝ እንጂ፣ እኔማ እንዲሁ የተቋጥሮ ዝምድና ይመስለኝ ነበር፤ አራት አምስት ቤት-ሩቅ። አሁን ሳየው ግን የሁለት የሶስት ቤት እንኳ ሆኖ አላገኘሁትም። እስከዚህ ቅርብ ናችሁ ማለት ነው- አንድ ቤት። ይገርማል! እኔ ጅሉ፣ እኔ ሞኙ ይኼን ወትሮ አላውቅም ነበር። ያወቅኩት ገና አሁን ነው- ከልደታው ተደጋጋሚ ዘመቻ ወዲህ።

ብቻ ዝምድናችሁ ሁለት ቤትም ይሁን አንድ፣ ቁንጮው የኢሕአዴግ ባላባት፣ ትልቁ ሰው መለስ፣ በሕይወት እያሉ፣ ባገር እያሉ ስንት ሱሪ የታጠቀ ወንድ ነው፣ ለአንድ ሰው ለእርስዎ ለአባ ጳውሎስ ሲል ሕገ መንግስቱን የሚጥሰው? እስከዚህስ የሚሰቀጥጥ ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ረገጣ የሚያደርሰው? በማለት እንደ መፎከርም ቃጥቶኝ ነበር- እኔ ሞኙ።

አዎን እሳቸው ባገር ቢኖሩም ባይኖሩም፣ አሁን ማ ይሙት እጅሬ ሳያውቁት፣ እጅሬ ሳይፈቅዱ እንዲህ ያለው ድርጊት- ያውም በሰላማዊ ዜጎች ላይ፣ ያውም በታፈረ በተከበረ በአምልኮ ስፍራ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ብዬም ተገርሜ ነበር- እኔ ሞኙ፤ እኔ ተላላው።

እንዲያው እኒህ ሰው በሆነ ነገር ተሸንፈው አድርገውት ይሆን? ወይ ደግሞ፣ «ሰራሴ ሰው ያልሆንኩ፣ ለማ ልሆን ነው? መደጋገፍማ አለብን» በማለት፣ እውቀው ሆን ብለው አድርገውትስ ከሆነ ብዬም እስከ ማሰብ ደርሻለሁ- ሲጨንቀኝ።

አዎን፣ ይህ ያልኩት እውነት ሆኖ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ይህን እኩይ ድርጊት ለአንድ ሰው ለእርስዎ ለአባ ጳውሎስ ሲሉ አድርገውት ከሆነ፣ ዕንባን ወደ ላይ እየረጩ «ይታይኽ! አዎን ይታይኽ!» ከማለት፣ የግፉ ጽዋ እስኪሞላ ድረስ፣ አንገትን ደፍቶ በሕእግስቱ ከመጠበቅ ወዲያ ምን ማድረግ ይቻላል?- «አባታችን»።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሸንጣጣውን ገትረው ለእርስዎ እንዲህ መቆማቸውን ሳየው፣ ነገሩ ይደንቀኛል። የሚረዳ፣ የሚጠቅም ሹነኛ ሰው ሲፈለግ፣ ሰውና ሰውን፣ ሰውና እግዚአብሔርን የሚያቀራርብ፣ የሚያግባባ ይልቁንም ከባድ ነገር ቢፈጠር በእቦ በስላሴ ብሎ የሚያስማማ፣ የሚያስታርቀውን ሰው ይፈልጉታል እንጂ፣ እንኳን ለሌላ ለራሱ የማይሆነውን፣ እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ ከራሱም ከሌላውም ጋር የሚጣላውን፣ አሁን ሰው አሁን ሌላ የሚሆነውን፣ እንዲህ እንደ እርስዎ ያለውን ሰው ምን ያደርግልኝ? ምንስ ይጠቅመኝ ብለው ነው እስከ ዚህ ጋሻ መከታ ሊሆኑዎ የበቁት? ስንት ሰው እያለ?- አሳዘኑኝ መለስ። ይኼ፣ «የትልቅ ሰው መሳሳት ተራራ ያህላል» የሚባለው እውነት ነው ልበል?

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ በልደታ- መድኃኔ አለም ላይ የተከፈተው ዘመቻ በአንድና በሁለት ዙር ብቻ ያበቃ አልነበረም፤ በቅፅረ ቤተክርስቲያንም ብቻ የተወሰነ አልነበረም። የቀበሌ አዳራሽ ተከራይተው፣ ለወረዳ ፖሊስ አመልክተው የጽዋ ማሕበራቸውን በዓል፣ እንደ ወጉ፣ እንደ ስርአቱ በስባሔ፣ በዝማሬ በሚያከብሩት፣ የሰንበት ትምሕርት ቤት ወጣቶችና በተጋባዥ እንግዶቻቸው ላይ የወረደ፣ መፈጠርን የሚያስጠላ ሌላ ገዐር፣ ሌላ ሰቆቃ፣ ሌላ ዋይታ ያስከተለ እኩይ ድርጊት ነበር።

«አባታችን» ይኼ ሁሉ ግርግር ማንነትዎ በሚገባ እንዲታወቅ፣ ስልጣንዎ እንዲረጋገጥ፣ ኃያል ክንድዎ እንዲታይ ለማድረግ የተሞከረ የተዘከረበት እኩይ ድርጊት መሆኑን ሁሉም ያወቀው ነገር ነው፤ አዎን ልደታ ምሳሌ መሆን አለባት- እኔን ያየህ ተቀጣ፤ ግርግር ሳይኖር፣ የስላም መታወክ ሳይኖር ፖሊስስ እንዴት ታዘዘ? ያን ዓይነቱ ከመጠን ያለፈ መከራና ስቃይስ እንዴት ደረሰ? ይህ እንግዲህ ቁልጭ አድርጎ ያሳየኝ- ልበል ያረጋጠልኝ- «ቅዱስነትዎ» ለይስሙላ፣ ለማስመሰል በቤተ ክርስቲያኒቱ መንበር ላይ የተቀመጡ፣ ሁለተኛው የኢሕአዴግ ሰው መሆንዎን ነው- ለእኔ ለራሴ።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ እንደ እውነቱ ከሆነ በእርስዎ እጅ ወይም በእርስዎ፣ «በቅዱሱ ፓትርያርካችን» ምክንያት እንዲህ ያለውን መከራና ስቃይ መቀበል እጅግ ሞታደል ነው፤ በኔሮን፣ በዲዮቅልጢያኖስ እጅ ከመቀበል ይልቅ ይህኛው የበለጠ ጸጋ፣ የበለጠ ክብር የሚያሰጥ ነውና።

እስከ መጨረሻው ድረስ ፀንታችሁ የተገኛችሁ እናንተ የልደታ- መድኃኔ ዓለም ገዳም ካህናትና ዲያቆናት፣ የሰንበት ትምሕርት ቤት ወጣቶችና ምእምናን፤ ስለ ርትዕት ሃይማኖታችሁ፣ ስለ እውነትና ጽድቅ ብላችሁ፣ እንዲህ ያለውን መከራና ስቃይ በጽናት፣ በትእግስት ተቀብላችኋልና ምንኛ ታድላችኋል?- እቀናባችኋለሁ።

እናንተ እስከ መጨረሻው ጸንታችሁ የተገኛችሁ ልደታ- መድኃኔ አለሞች፣ ደስ ይበላችሁ! ስማችሁ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም መዝገብ በወርቅ ቀለም ተጽፏልና- አዎን ደስ ይበላችሁ፤ ምስጋናም ይገባችኋል።

«ብፁዕ ወቅዱስ» ፓትርያርክ፣ ስልጣንዎን መከታ አድርገው፣ ከበስተኋላዎም የተማመኑትን ተማምነው በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ የፈፀሙት በደል አንድና ሁለት የለውም። ከሁሉም ከሁሉም የሚከፋው ግን፣ የቤተ መቅደሶቹ መዘጋት ነው። አዎን፣ ቃለ እግዚአብሔር እንዳይነገርባቸው፣ ስብሐተ ነግህ እንዳይደርስባቸው፣ ሰዓታት፣ ማኅሌት እንዳይቆምባቸው፣ ሥጋሁ ወደሙ እንዳይፈተትባቸው ቤተ መቅደሶቹን በመዘጋትዎ፣ ታሪክ፣ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ የነበረው፣ አብያተ ክርስቲያናትን በአዋጅ የዘጋው፣ ከመከራው ጽናት የተነሳ ዘመኑን ዘመነ ሰማዕታት ያሰኘው፣ የአረማዊው ንጉስ (ቄሣር)፣ የዲዮቅልጥያኖስ ማክሰኛ አድርጎዎታል፤ ታሪኝ፤ ኢሣኝ።

ጳውሎስ ዳግማዊ ዲዮቅልጥያኖስ- ሌላ ስም-አረማዊ ግብርን ተከትሎ የወጣ፤ አዎን ጳውሎስ ዳግማዊ ዲዮቅልጥያኖስ- ፀላዊ ጳጳስ።

«አባታችን» «ብፁዕ ወቅዱስ» የሚለውን ክቡር ስም አፌ ቁርጥ እስኪል ድረስ እየጨመርኩ፣ እየደጋገምኩ የቀጠልኩልዎ ሕይወትዎ የብፅዕናን የቅድስናን ግብር የተላበሰ ሆኖ ነው ብዬ ሳይሆን- እርስዎ ራስዎ ነኝ እንደማይሉ እርግጠኛ ነኝ- በእናት ቤተ ክርስቲያኒቷ መንበር ላይ ስለተቀመጡ ብቻ የእርሷን ክብር ለመጠበቅ ስል መሆኑን እንዲያውቁልኝ እፈልጋለሁ።

በዚህኛውም ሆነ ከዚህ በፊት በተከታታይ በወጡት ኢትኦጵ መጽሔቶች (ቅጽ 4/ ቁጥር 044 እና ቁጥር 045) እንዲሁም ከዚያ አስቀድሞ በጦማር ጋዜጣ አከታትዬ በቅርብኳቸው ጽሁፎች ላይ የገለጽኳቸው ነገሮች እንዲሁ (በከንቱ) ስም ለማጥፋት የቀረቡ ወይም ተራ አሉባልታዎች ሳይሆኑ፣ ራስዎ በትክክል የፈጸሟቸው እኩይ ድርጊቶች ለመሆናቸው በቂ ማስረጃ አለ።

ስለዚህ ይህ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ቢጠራኝ ቀርቤም ለማስረዳት፣ ለምናልባቱ- እዎን እንዲያው ለምናልባቱ- ድንገት የትላንትና ነገር ኖሮ የሚያሳምነኝ ከሆነም (ካለ)፣ ወድቄ ተንከባልዬ ይቅርታ ለመጠየቅ፣ ንስሐም ለመግባት ዝግጁ መሆኔን በቅድሚያ ልገልጽ እወዳለሁ።■

## «መረጃ...

(ከገፅ 34 የዞረ)

**ኢትኦጵ፦ የመጨረሻው የችግሩ መፍትሔ ምንድ ነው?**

ዶ/ር ነጋሶ፦ መፍትሄው በሁለቱ አገር የሚታይ ነው። አንደኛው ያጣዐቢያ መንግስት ቢቀበለውም ባይቀበለውም ሊነገረው የሚገባ አብይ ቁም ነገር አለ። ኤርትራ ነፃነቷን ስታገኝ፣ ለራሷ የሚገባት ይዞታ አለ። ይህም በ1902 ና በ1908 ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዥዋ ጣሊያን ጋር ውል የገባችበት ብቻ ነው። ከ1902 ና 1908 ወዲህ የጣሊያን መንግስት የያዘውን የኢትዮጵያ መሬት መሠረት አድርጋ መከራከሩ አይጠቀማትም። የኢትዮጵያ የሆኑ ከጥንት ጀምሮ ስታስተዳድራቸው የነበሩና የኤርትራ ሕዝብም በሚገባ የሚያውቃቸው ይዞታዎች ላይ ያለትን የይገባኛል ጥያቄ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማንሳት ይኖርባታል። ኢትዮጵያን ለማበሳጨት ስትል ብቻ በኢትዮጵያ መሬቶች ላይ ከምታደርገው ትንኮሳ መታቀብ አለባት። ይህንንም የኢትዮጵያ ዕወቅና ሌሎች መንግስታትም በጥሞና ሊረዱት ይገባል። ኮሚሽኑም ስህተት ከፈፀመ ከሚቀርብለት መረጃ ተነስቶ ሊያስተካክለው ይገባል። ኮሚሽኑ እምቢተኛ ሆኖ በስህተቱ ከገፋበት የፀጥታው ም/ቤት ሁኔታውን ጣልቃ ገብቶ ሊያየውና ሊያሸሽለው ይችላል። በዚህ መልኩ የድንበር ማካለሉ ተጠናቆ ወደ ሰላም መግባት ይቻላል።

ሌላው የኢትዮጵያ መንግስት የእኛ የሆነውን ይዞታ፣ ለዚያውም ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለበትን መሬት በብላሽ ልንለቅ አይገባም ሲል መከራከር አለበት። ሰላም እይኖርም ወይንም ዓለም አቀፍ እርዳታ እናጣለን በሚል የራሳችን የሆነውንና ዛሬም በእኛ ስር ያለውን ይዞታችንን የማስከበር ግዴታ አለበት። ምናልባት ይህ ባይሆን ጦርነት ሊቀሰቀስ ይችላል ወይ? ለሚለው ከእንግዲህ ወደ ጦርነት መሄድ የለብንም። በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተከራክረን ይዞታችንን በማስመለሱ ተግባር ላይ ነው ማተኮር ያለብን። ይህ እንግዲህ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። ምርጫችን ግን ይህ ነው መሆን ያለበት። ይዞ ሕጋዊ ተግባራችን ሆኖ ሳለ ኤርትራ ጦርነት ከቀሰቀሰች የሚል ስጋት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን እኛ ወደጦርነት ገብተን ይዞታችንን አስከብረናል፤ ከድንበር አልፈን የደዝናቸውን የኤርትራ መሬቶች መልሰናል፤ በዚህ መሃል 25 ኪሎ ሜትር አለ።

የፀጥታው ም/ቤት ሰላም አስከባሪ ኃይል ሰፍሮበታል፤ ይህ ባለበት ሁኔታ ኤርትራ ጦርነት መቀስቀስ➔



ጟ - እኔ ያሰብኩት ፡ ግልሆነ፤ እኔ፡ ያልኩት [illegible]
ለምን፡ [illegible]